**የአውደ ጥናቱ አዘጋጆች፡-** መልካሙ ኦጐ የሕግ ቢሮ ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ጋር በመተባበር

**የአውደ ጥናቱ ርዕስ፡-** የጥፋተኝነት ድርድር እና አማራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶች በኢትዮጵያ ሪቂቅ የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ

**ቦታ፡-** ካፒታል ሆቴል

**ቀን፡-** ኅዳር 2 እና 3 ቀን 2010 ዓ.ም.

## አቶ አመሃ መኮንን - መድረክ አመቻች

የዚህ አውደ ጥናት ዋና ዓላማ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓታችን ውስጥ ዘመናዊ እና ባሕላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶች እነማን ናቸው ችግሮቹስ ምንድ ናቸው የሚለውን እና ምን ዓይነት አማራጭ የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች በረቂቅ የወንጀል ሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ ውስጥ መካተት አለባቸው በሚሉ አጀንዳዎች ላይ ውይይት የምናደርግ ሲሆን የእኔ ኃላፊነት ሥልጠናውን የማመቻቸት ሲሆን አውደ ጥናቱን ያዘጋጀው መልካሙ ኦጐ የሕግ ቢሮ ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ጋር በመተባበር ነው ብለዋል፡፡ ይህን አስቦ ተነሳሽነቱን ወስዶ አውደጥናቱ እንዲዘጋጅ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረከተው የመልካሙ ኦጐ የሕግ ቢሮን እንዲሁም የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበርን እንዲሁም በፋይናንስ ያገዘንን የአሜሪካ ኤምባሲን አመሰግናለሁ ብለዋል፡፡ በመቀጠልም የበጐ አድራጐት ማኅበራት ሕግ በማኅበራቱ የገንዘብ አቅም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የፈጠረ በመሆኑ ይህ ዓይነት አካሄድ ችግሩን ለመፍታት መፍትሔ ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡ በመቀጠልም የፕሮግራሙን ሥነሥርዓት ካስተዋወቁ በኋላ የመክፈቻ ንግግር እንዲያደርጉ አቶ መልካሙ ኦጐን ወደመድረኩ ጋብዘዋል፡፡

## አቶ መልካሙ ኦጐ

አቶ መልካሙ ኦጐ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸውን በእንግሊዝኛ ቋንቋ ካስተላለፉ በኋላ የአውደጥናቱ ዋነኛ ዓላማ በረቂቅ የወንጀል ሥነሥርዓት እና የማስረጃ ሕጉ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመጠቆም እና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ እንዲሁም በዘርፉ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላት ስለረቂቅ ሕጉ ይዘት እንዲተዋወቁ ለማድረግ ሲሆን ለሁለት ቀን በሚቆየው አውደጥናት ላይ ሰባት ጽሑፍ አቅራቢዎች የሚሳተፉ ናቸው ብለዋል፡፡ አውደጥናቱን እንድናዘጋጅ ይረዳ ዘንድ የገንዘብ ድጋፉን ያደረገልን የአሜሪካ ኤምባሲን በማመስገን የአውደጥናቱን መከፈት በይፋ አብስረዋል፡፡

## ሚስ አሌክሳንድር ፎስተር - ከአሜሪካ ኤምባሲ

ሚስ አሌክሳንድር ፎስተር ከአሜሪካ ኤምባሲ እንዲሁም በአሜሪካ የቀድሞው ዐቃቤ ሕግ በመሆን ያገለገሉ ስለመሆናቸው ገልፀው አቶ መልካሙን ኦጐን ያገኙበትን አጋጣሚ እንዲሁም በአዲስ መልክ እየተሻሻለ ስላለው የወንጀል ሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ መረጃው ያላቸው መሆኑንና ይህንኑ ለማስተዋወቅ ይረዳ ዘንድ ይህን አውደጥናት በገንዘብ ለመደገፍ እንዲሁም የአሜሪካ ልምድ እና ተሞክሮን ለተሳታፊዎቹ ለማስተዋወቅ ዝግጅት ያደረጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

## አቶ አምሃ መኮንን - መድረክ አመቻች

በመቀጠልም የተሳታፊዎች ትውውቅ እንዲደረግ ከጠየቁ በኋላ ሁሉም ተሳታፊ ስም እና የመጣበትን ተቋም እንዲሁም የሥራ ኃላፊነት በመግለጽ ትውውቁ ከተጠናቀቀ በኋላ የመድረክ አመቻቹ የተሳታፊዎች ስብጥር እጅግ በጣም ጥሩ መሆኑን ገልፀው ዐቃቤ ሕጐች፣ ዳኞች፣ የሕግ ምሁራን፣ የቀድሞ ዳኞች፣ ጠበቆች እንዲሁም በከፊል ፖለቲከኞች ጭምር የተገኙ በመሆናቸው አውደጥናቱ የተሳካ እንደሚሆን እምነታቸውን በመግለጽ ጭምር የመጀመሪያውን ጽሑፍ አቅራቢ አቶ ታምራት ኪዳነማርያምን ወደመድረክ ጋብዘዋል፡፡

## አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - ጽሑፍ አቅራቢ የኢሕባማ አባል እንዲሁም ጠበቃና የሕግ አማካሪ

ይህን ጽሑፍ እንዳቀርብ የሰየመኝን የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር(ኢሕባማ) እና መልካሙ ኦጎ የሕግ ቢሮን እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ ያደረገውን የአሜሪካ ኤምባሲን አመሰግናለሁ ብለዋል፡፡ በመቀጠልም ጽሑፍ አቅራቢው ጽሑፍ እንዲያቀርቡ ጥያቄ የቀረበላቸው እና ኃላፊነቱን የወሰዱት በአጭር ጊዜ ውስጥ በመሆኑ ጉድለት ቢኖርበት በዚሁ ምክንያት መሆኑን ለተሳታፊዎች አስቀድመው ገልፀው የሚያቀርቡት ጽሑፍ ለውይይት ዓላማ መሆኑን ጭምር አስታውቀዋል፡፡

ጽሑፍ አቅራቢው በቀጥታ በረቂት ሕጉ ላይ የተቀመጡትን አንቀጾች በመዳሰስ የጀመሩ ሲሆን በረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 10 በጠበቃ የመወከል የሚል ሲሆን በንዑስ ቁጥር 2(ለ) ሥር እንደተመለከተው የተከላካይ ጠበቃ የሚወከለው ከአምስት ዓመት በላይ ሊያስቀጣ በሚችል ወንጀል የተከሰሰ ሰው ስለመሆኑ የተቀመጠ መሆኑ ጥሩ ነው፡፡ ኢሕባማ የተከላካይ ጠበቃ ቢሮን በተመለከተ ያጠናው ጥናት መኖሩን ጠቁመው በአፍሪካ ደረጃ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን መኖሩን እና ኮሚሽኑ የተከላካይ ጠበቃ ያልተወከለበትን ፍርድ በሚመለከት አግባብነት የሌለው መሆኑን ጠቁሞ ሀገራት በእንደዚህ ዓይነት ጉዳይ ላይ ካሣ እንዲከፍሉ ጭምር እየታዘዘ ያለበት ሁኔታ እንዳለ ጠቁመዋል፡፡ በመቀጠልም በረቂቁ አንቀጽ 15 የተቀመጠው ድንጋጌ እውነትን ስለማውጣት መርህን ያስቀመጠ ይሁን እንጂ አሁን ባለው አሠራር ፖሊስ እና ዐቃቤ ሕግ የሚያደርጉት ትግል ክርክርን ለማሸነፍ ብቻ የሚመስል ሲሆን ያጠፋ ሰውን ሰብዓዊ በሆነ መልኩ ማስቀጣት ተገቢ ሆኖ ሳለ ነፃ የሆነን ሰው ለማስቀጣት ትግል ማድረግ የፍትሕ ሥርዓቱን የሚያደክም እና የማኅበረሰቡን እምነት የሚያሳጣ ነው ብለዋል፡፡

በረቂቁ አንቀጽ 18 የፍትሕ ተቋማት የወል እና የጋራ ኃላፊነት የሚል መቀመጡን እና በንዑስ ቁጥር 3 ሥር የፍትሕ አካላት ወይም ተቋማት እነማን እንደሆኑ በዝርዝር የሚያስቀምጥ ሲሆን እነዚህም ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ ተከላካይ ጠበቃ እና ፍርድ ቤቶችን ያጠቃለለ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ የግል ጠበቆች እና የጠበቆች ማኅበራት አለማከታተቸው አግባብ እንዳልሆነ ጠቁመዋል፡፡ በሌላ አግባብ ደግሞ ፍርድ ቤቶች በዚህ ዝርዝር ውስጥ መካተታቸው ከፍርድ ቤት ነፃነት ጋር የተዘያያዙ ችግሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ አንዳንዶች ከተግባር ጋር የሚያነሱ ስለመሆኑ ጠቁመዋል፡፡ በአንቀጽ 20 ንዑስ ቁጥር 4 ሥር ዐቃቤ ሕግ ለመከላከያ የሚጠቅም ማስረጃን ለፍርድ ቤት ወይም ለተከሳሽ አሳልፎ ሊሰጥ እንደሚችል መጠቆሙ ሊበረታታ የሚገባ እና ሙያውን ከፍ ያለ ክብር የሚያሰጥ ነው ብለዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በንዑስ ቁጥር 8 ሥር የተመለከተው ማረሚያ ወይም ማረፊያ ቤትን የመጐብኘት የዐቃቤ ሕግ ግዴታ ከእስረኛ አስተዳደር ጋር በተያያዘ መልካም እንደሆነ አድናቆታቸውን ገልፀዋል፡፡ ይህ ዓይነት አሠራር በደልን በአስተዳደር መልኩ ለመፍታት ጭምር ያስችላል፡፡

የቀድሞው የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ላይ የወንጀል ክስ(accusation and compliant) መፈረም እንዳለበት የሚያስቀምጥ ሲሆን ክሱ ሃሰተኛ ከሆነ የሃሰት ጠቋሚው በሥም ማጥፋት የሚጠየቅበት አግባብ ነበር ካሉ በኋላ አሁን በተሻሻለው ረቂት ሕግ ውስጥ ይህ ዓይነት ድንጋጌ አመለካተቱ መታየት አለበት ብለዋል፡፡ ከአንቀጽ 85 ንዑስ ቁጥር 4 ሥር በተመለከተው ድንጋጌ ስለ ብርበራ የሚያስቀምጥ ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ በተግባር የሚያጋጥመው ችግር የብርበራው ዓላማ እና የብርበራው ሥራ ሲከናወን ሰፊ የሆነ ችግር ያጋጥማል፡፡ በምሣሌነት መኪና በመያዝ መሳቢያ መበርበር ተገቢ አለመሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በርበራም ሲደረግ በምስል እና በድምጽ ጭምር ቢቀረጽ መልካም እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ሌላው ለውጥ በሕጉ ላይ የተመለከተው ኤግቢት አያያዝ እና አመላለስን በተመለከተ ሰፋ ያለ ነገር መቀመጡ ተገቢ ነው፡፡ ቀደም ብሎ በነበረው ሕግ ላይ ስለአመላለስ በተመለከተ የቀረበ ዝርዝር ነገር አልነበረም፡፡ ከእዚህ በተጨማሪ ቀደም ባለው ጊዜ ዋስ አስይዞ ንብረት የመልቀቅ አሠራር በዐቃቢ ሕግ መሥሪያ ቤት ያለ ሲሆን ይህ አሠራር በሕግ ድጋፍ ቢያገኝ መልካም እንደሆነ ጠቁመው በአንቀጽ 93 የተመለከተው የተጠርጣሪን የፋይናንስ እንቅስቃሴን በተመለከተ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል የሚል

አንቀጽ ያለ ሲሆን ይህ ትዕዛዝ በፍርድ ቤት ወይንስ በመርማሪ እና በዐቃቢ ሕግ የሚሰጥ ስለመሆኑ ግልጽ አይደለም፡፡ በአንቀጽ 94፣ 95 እንዲሁም 112 ላይ የተቀመጡት ድንጋጌዎች ጥሩ መሆናቸውን ገልፀው በአንቀጽ 120 ንዑስ ቁጥር 3 ሥር የተመለከተው በፖሊስ ጣቢያ የሚሰጠው ቃል በማስረጃነት ፍ/ቤት ባይቀርብ የሚል ሃሳብ አንስተዋል፡፡ ከእዚህ በተጨማሪ በአንቀጽ 123 ሥር የተመለከተው ተጠርጣሪን በ48 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ማቅረብ የሚለው የመጓጓዣ ጊዜን ሳይጨምር አሁን ባለንበት ሁኔታ የተሻለ መሠረተ ልማት እና የፍርድ ቤቶች ተደራሽነት ባለበት ወደ 24 ሰዓት ዝቅ ቢደረግ የተሻለ እንደሆነ ጠቁመው ያለ ዋስትና መልቀቅ የሚቻልበት የሕግ አግባብ ቢካተት መልካም እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

በአንቀጽ 124 ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ የተቀመጠው ለመካከለኛ ወንጀሎች 28 ቀን እንዲሁም ከሽብር ጋር የተያያዙ ወንጀሎች ከ4 ወር መብለጥ እንደሌለበት መካተቱ መልካም ሆኖ የጊዜ ቀጠሮ መዝገብ መዘጋት ውጤት ምንድን ነው የሚለው በግልጽ ሊመለከት ይገባል ብለዋል፡፡ በጊዜ ቀጠሮ ላይ ያለ እና በፍ/ቤት ማረፊያ ቤት እንዲቆይ የታዘዘ ሰው የጊዜ ቀጠሮው ቢዘጋ ማረፊያ ቤት ተጠርጣሪው እንዲለቀቅ ትዕዛዝ ስለማይደርሰው ብዙ ጊዜ ሊታሰር እና ያለአግባብ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ የሚደረግበት ልምድ ያለ በመሆኑ ይህ ጉዳይ የሕግ መፍትሔ ሊሰጠው እንደሚገባ አበክረው ገልፀዋል፡፡

ዋስትናን በሚመለከት ከፀረ ሽብርና ከፀረ ሙስና አዋጅ ውጪ ቀደም ብሎ በነበረው ሥነ-ሥርዓት ሕግ ዋስትና የሚነፈገው በአንቀጽ 63 እና/ወይም 67 መሠረት በተቀመጡት ሁኔታዎች ነው፡፡ በዋስ ከሥር የመፈታት መብት በሕገ መንግሥቱ ላይ የተቀመጠ ሲሆን ይህ መብት በሕገ-መንግሥቱ ገደብ የተበጀለት ሲሆን ይህ ልዩ ሁኔታም በጠባቡ መተርጐም አለበት፡፡ አሁን ያሉት ሕጐች ዋስትና መብት ስለመሆኑ የሚያሳዩ አይደለም፡፡ ዋስትናን ስለመገደብ ለፍ/ቤት ሥልጣን መስጠት የተሻለ ይሆናል ያሉት ጽሑፍ አቀራቢው ዋስትናን ከመከልከል ይልቅ ሌሎች አማራጮችን መቃኘት አግባብ እንደሆነ ጠቁመው በምሳሌነትም ከአገር እንዳይወጣ ማገድ በፖሊስ ጣቢያ በየቀኑ እየቀረቡ ማስፈረም ወዘተ… አማራጮችን አስታውሰዋል፡፡ በግምገማቸውም በቀድሞ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 63 መሠረት የተቀመጠው የተሻለ ነው የሚል እምነት አለኝ ብለዋል፡፡ ከእዚህ ባሻገር በረቂቁ አንቀጽ 156፣ 161፣ 170 እና 174 ጥሩ ማሻሻል ተደርጉባቸዋል፡፡

በመጨረሻም በረቂቁ 176 ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ክስ አለመመሥረት በሚመለከት የጥፋተኝነት ድርድር ከሚባል የእምነት ክህደት ክርክር ቢሆን የተሻለ አይደለም ወይ የሚል አስተያየት አለኝ፡፡ የማስረዳት መጠንን እና ሸክምን በተመለከተ በተለያዩ ሀገራት የሕግ ሥርዓቶች ከጥርጣሬ በፀዳ መልኩ ማስረዳት ወይንም ደግሞ በቂ እና አሳማኝ ማስረጃ ማቅረብ የሚለውን ምጣኔ የሚከተሉ ሲሆን የአውሮፓ ሀገራት የማጣራት ዘዴ እውነትን ለመፈለግ የሚደረግ ጥረት ሲሆን በኮመን ሎው ደግሞ ትኩረቱ የክርክር ሚዛን ላይ ነው፡፡ የእኛ አገር ልማድን ስንቃኝ ፖሊስ በአንድ ወገን ላይ ያለ ዶሴ ከፍቶ የመመርመር ሁኔታ እና ማስረጃዎችን ለክስ በሚያመች ሁኔታ የማሰባሰብ ኋላም ክር የሚቀርበው ትልቅ ከሆነው ከዐቃቤ ሕግ ተቋም ጋር በመሆኑ የሙግቱ ሸክም በተከሳሹ ጫንቃ ላይ የሚያርፍ በመሆኑ ለእኛ አገር የሕግ ሥርዓት የምንመርጠው የማስረዳት ምጣኔ እና ሸክም ይህን እውነታ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆን መቻል አለበት በማለት ጽሑፋቸውን ቋጭተዋል፡፡

## <u>አቶ አምሃ መኮንን - መድረክ አመቻች</u>

የወንጀል ፍትሕ ሥርዓታችን ብዙ ጉድለት የነበረበት በትምህርት ቤትም ሆነ በተግባር የምንመለከተው ጉዳይ ነው፡፡ በትክክል ወንጀል ፈፃሚዎችን ለይቶ በተፋጠነ ሁኔታ ውሳኔ የመስጠት ነገር ደካማ ነው፡፡ ረቂቅ የወንጀል ሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕጉ አንዳንድ የሰለጠነ ሃሳቦችን ያካተተ ቢሆንም አሁንም ቢሆን የቀሩ እና በድጋሚ መታየት ያለባቸው ነጥቦች ስለመኖራቸው ጽሑፍ አቅራቢው ለመጠቆም ሞክረዋል፡፡ በጠበቃ የመወከል መብትን በተመለከተ በሕገ መንግሥቱ ላይ የተቀመጠው 'miscarriage of justice' የሚለው መስፈርት ለፍርድ ቤቶች ቢተው ጥሩ ነው፡፡ ያሁኑም ሆነ የቀድሞው ሥነ-ሥርዓት ሕጐች ከሕገ-መንግሥቱ ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም ብለዋል፡፡

የመደራደር አቅም እኩልነት በሚመለከት ከሳሽ ዐቃቤ ሕግ የምስክሮችን ዝርዝር ለተከሳሽ አላሳውቅም የሚልበት ሁኔታ በተግባር የሚታይ ሲሆን ተከሳሽ ክስ እና ማስረጃ ሊደርሰው ይገባል የሚለውን መርህ የሚጣረስ ነው ያሉት መድረክ አመቻቹ ዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን አልገልጽም የሚለውን ጉዳይ በተመለከተ በፍ/ቤት ተነሳሽነት ለሕገ-መንግሥት አጣሪ ኮሚቴ ቀርቦ የነበረ ቢሆንም የሕገ-መንግሥት ጥያቄ አያስነሳም በሚል ምክንያት የተዘጋ ስለመሆኑ ጠቁመዋል፡፡

የዐቃቤ ሕግ እና የፖሊስ ተቋማት አንድን የተጠረጠረ ሰው ሊያስወነጅል እና ሊያስቀጣ የሚችለውን ማስረጃዎች በማፈላለግ ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ሲሆን በተከሳሽ በኩል የሚቀርቡ እና ሊጠቅሙ የሚችሉ ማስረጃዎችን የማሰባሰብ ሁኔታ ፍፁም አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡ ጠበቆች የፍትሕ ሥርዓቱ ናቸው ይባል እንጂ ቀደም ብሎ በነበረውም ሕግ ሆነ በአዲሱ ረቂቅ ሕግ ላይ ይህ ስለመሆኑ ከአፍ የዘለለ እርምጃ መወሰድ አልተቻለም፡፡ ጠበቃው የተቃና የፍትሕ ሥርዓት እንዲኖር የበኩሉን አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆኑ የታመነ ቢሆንም የፍትሕ አካል ሆነ በሕጉ አለመቀመጡ የራሱ በጐ ያልሆነ ተፅዕኖ የሚፈጥር መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

የጠቋሚዎች እና የምስክሮች ጥበቃ በአዋጅ መልክ ወጥቶ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ የተከሳሾች ምስክር በሚመለከት ጥበቃ እና ከለላ የሚሰጥ ወይንም ይህንኑ የሚመለከት ምንም የተባለ ነገር የለም፡፡ የዋስትናን ጉዳይ በተመለከተ የሙስና ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ወይንም ተደራራቢ ክስ በሆነ ጊዜ ቅጣታቸው ተደምሮ ዋስትና የሚከለከልበትን ሁኔታ በሕጉ የተመለከተ ይሁን እንጂ አሁን ያለው የሕግ አወጣጥ ዋስትናን በሚመለከት ከሕገ-መንግሥቱ ጋር የማይጣጣም ነው፡፡ ከዚሁ አዋጅ ጋር በተያያዘ በተደራቢነት የተፈፀመ ወንጀል ከሙስና ወንጀል ውጪ የሆነ ወንጀል ቢሆን በተደራቢነት ይደመራል ወይስ አይደመርም የሚል አጠያያቂ ነው ካሉ በኋላ ለጥያቄ እና አስተያየት መድረኩን ክፍት አድርገዋል፡፡

## <u>አቶ ፋሲል ስለሺ - የኢሕባማ አባል</u>

ይህቺ አገር ረቂቅ ሕግ የማውጣት ችግር የለባትም፡፡ ለአብነትም የንግድ ሕጉ የአማራጭ ግጭት መፍቻ መንገዶች የማስረጃ ሕግ ወዘተ… መጥቀስ ይቻላል፡፡ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሕጐችን ሲያረቅቅ ምሁራን አለማማከሩ ሕጉ ፀድቆ ሲወጣ በተግባር የሚታዩ ችግሮች ፈጥጠው እንዲወጡ ምክንያት ሆኗል ካለ በኋላ ረቂቁ ያለአግባብ ለታሠሩ ሰዎች ካሣ ስለሚከፈልበት ሁኔታ ሊደነገግ ይገባው ነበር፡፡ ያለአግባብ የታሠረው ሰው ሞራላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል፡፡ በምርመራ ላይ መሪ ጥያቄ ምንድን ነው የሚለው ግልጽ አይደለም፡፡ የኢግዚቢት ዓላማ እና ምንነት መብራራት አለበት ብለዋል፡፡

## <u>አቶ ስሜነህ ኪሮስ - የኢሕባማ አባል</u>

የወንጀት ሥነ-ሥርዓት ሕግ ረቂቅ በደርግ ዘመን በሶሻሊስት ሥነ ምግባር ወጥቶ የነበረ ሲሆን በ1990ዎቹ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ነበር፡፡ ይህ ዓይነት ስብሰባዎችም በብዛት ተደርገው ነበር፡፡ ጽሑፍ አቀራቢው ያቀረቧቸውን ነጥቦች የምስማማበት ሆኖ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ውጤታማ እንዲሆን የመጀመሪያው ነጥብ የማስረዳት ግዴታ እና ሸክም በሚመለከት ጥርት ያለ አቋም ሊኖር ይገባል የማስረዳት ሸክም ወደተከሳሽ አዙሯል፡፡ ምክንያቱም አሁን ያሉት የእኛ አገር ውሳኔዎች ተከሳሽ የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ ማስተባበል ስላልቻለ ጥፋተኛ ብለናል ነው እንጂ የሚለው ዐቃቤ ሕግ ተከሳሽ ወንጀል ስለመፈፀሙ ያረጋገጠ በመሆኑ ነው የሚል አይደለም፡፡ በስህተት ጥፋተኛ የተባለን ሰው የምንክስበት የመፍትሔ አቅጣጫ ሆነ አግባብ የለንም፡፡ ሌላው ዋስትናን በሚመለከት ሕገ መንግሥቱ ዋስትና መብት ነው በሚል የደነገገበት አግባብ ያለ ሲሆን የሚገደብበትንም ሁኔታ በሕግ እንደሚወሰን የሚያስቀምጥ ሲሆን ይህም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ አንቀጽ 67 ሀ እና ሐ ሥር እንደተመለከቱት ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ መብት በአዋጆች ለአብነትም የፀረ ሙስና ወዘተ እየተሸረከረ ሕገ መንግሥቱን መና አስቀርቶታል፡፡ የእኛ አገር የሕግ ሥርዓት የኮመን ሎው እና የሲቪል ሎው ሥርዓቶች ድቅል ነው፡፡ ስለዚህ ከጥርጣሬ በፀዳ መልኩ ወይንም ደግሞ ግልጽና አሳማኝ የሚለውን ለጊዜው ትተን አንድን ሰው

ጥፋተኛ ነው ብለን ስንቀጣ ውስጣችን ወንጀል ስለመፈፀሙ እርግጠኛ ሆነን እና ሕሊናችንን ሳይቆረቁረን ስለመሆኑ ማረጋገጥ ተገቢ ነው።

## የዓለምታሪክ - ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

ተከሣሽ በሌለበትን የሚታዩ ጉዳዮችን አስመልክቶ ቀላልወንጀሎች እንዲወጡ መደረጉ አግባብ መሆኑን ጠቁመው በሕግ መሠረት የሚከለከል ዋስትናን በተመለከተ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን ጀነራል ኮሜንት 32 ላይ ዝርዝር ነገሮች የተቀመጡ ስለመሆናቸው አስረድተው ተከሳሽ በመጥሪያ ያልመጣ እንደሆነ በሀገር ልዕዋላዊነት ሥልታንን የሚገፋ እንደሆና አስቀምጠው በወንጀል ጉዳዮች ላይ በተለይ ፍትሓዊ የሆነ የክስ ሂደትና የተከራካሪ ወገኖች የድርድር አቅምን ማመጣጠን አስፈላጊ እንደሆነ በመተንተን አስረድተዋል። ከሕግመንግሥት ትርጓሜ ጋር በተያያዘ ሁሉም የህግ ባለሙያ ሕገመንግስቱን ጨምሮ ሌሎች ሕጎችን በመተርጎም ነው ሥራ ላይ የሚያውለው ስለሆነም ከፌዴሬሽን ምክር ቤት የሥልጣን ክልል ውጭ ባለው ላይ ሥነሕግን ለማሰደግ ሁሉም ባለሙያ ተገቢውን ትጋት ማሳየት እንዳለበት ገልፀዋል።

## አቶ ቴዎድሮስ ምህረት - ኢሕባማ ፕሬዝዳንት

የማኅበሩ ፕሬዝዳንት በረቂቅ ሕጉ በዚህ መድረክ ላይ የሚቀርበውን ሃሳብ ይበልጥ በማጠናከር ሃሳብና አስተያየቶች ለሚመለከተው የመንግሥት አካል እንደሚያቀርቡና ማኅበሩም በሕጉ ላይ ያለውን አስተያየት በግብኣት መልክ እንዲያስገባ የተጠየቅን በመሆኑ ይህን መድረክ አንደናው የግብዓት ማሰባሰቢያ በማድረግ የሚገለገሉበት መሆኑን ገልፀዋል።

## አቶ አመሃ መኮንን - መድረክ አመቻች

ረቂቅ የሥነሥርዓት ህጉን ለማዘጋጀት መጠነሰፊ ጅምሮች ተወስደው መሠራታቸውን አስታውሰው መዘግየቱ በራሱ ጎጂ እንዳልሆነና በሥነሥርዓቱ ላይ የሚካተቱት ድንጋጌዎች መሠረታዊ ቁምነገሮች እንደሆኑ ልብ ሊባል እንደሚገባ ጠቁመዋል። የሥነ ሥርዓት ሕጉ ከሰዎች መብት እና ነፃነት ጋር በእጅጉ የተቆራኙ መሆናቸው የተዋጣለት ዘመናዊ እና የሰለጠነ እንዲሆን ካስፈለገ በደንብ ጊዜ ተሰጥቶት ሊታይ ይገባል። የሁሉም የባለድርሻ አካላት ግብዓትን ይፈልጋል ብለዋል። ካሳን በተመለከተ ተገቢ ባልሆነ ማስረጃ ተከሶ ጉዳት የደረሰበት ሰው ካሳ የሚጠይቅበት የፍትሐብሔር ሥርዓት ያለ ሲሆን ነፃ ለወጣ ሰው ሁሉ የሚከፈል አይደለም የሉት አቶ አመሃ የክስ ሂደት ሙግት ያለበት እና አንዱ ረቺ ሌላው ተረቺ በመሆኑ የረታ ሁሉ ይካሳል ማለት ግን አይደለም። እያንዳንዱን ነገር በመደበኛው የፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ማስገባት ቀላል እንዳልሆነ ገልፀዋል።

## አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - ጽሑፍ አቅራቢ

አንድን ሰው ተከሶ ጥፋተኛ ስንል ህሊናችንን የማይቆረቁረን እንደሆነ ችግር የለውም ይህም ነው መመዘኛው ላይ የተቀመጠው ብለዋል። በሲቪል ሎው ሀገራት የክስ ሂደት እውነት ላይ ሲደረስ ብቻ ነው ክስ የሚቀርበው በኛ ሀገር ያለው ልማድ ግን ተከሳሽን ወደ ጎን በመተው የግል ተበዳይ ብቻ በሚያቀርበው ሃሳብ ምርመራ የሚካሄድ በመሆኑ ውጤቱም አደገኛ ይሆናል። በፍ/ቤትም ቢሆን በአብዛኛው ጊዜ ተከላከል የሚባለው ወንጀል ስለመፈፀም አለመፈፀም ጥርጣሬ እያለ መሆኑ ከመመዘኛው ጋር ግጭትን ይፈጥራል። አንድ ተከሳሽ ጉዳዩ በሌለበት ሲታይ የመሰማት እና የመከላከል ሕገ መንግስታዊ መብቱ ታልፎበት በመሆኑ በክስ አቅራቢው ወገን በተከሳሹ ላይ ክስ የቀረበበት ስለመሆኑ በትክክል መጥሪያ እንደደረሰውና እንዲያውቅ ከተደረገ በቂ ነው ብለዋል።

## አቶ ኑሩ ሠይድ - ጽሑፍ አቅራቢ

አቶ ኑሩ ሠይድ በዋናነት በረቂቅ ሕጉ ላይ ያላቸውን ትችት የሚያቀርቡ መሆኑን ገልፀው ቀደም ብሎ የነበረውን ሕግ ትተው ወደአዲሱ ለመምጣት ምክንያት የሆነው ነገር በረቂቅ ሕጉ ላይ

በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ሕጉ የተሻሻለበት ዋነኛው ምክንያት ወይም ዓላማ የሠለጠነ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ እንዲኖረን እንዲሁም ቀልጣፋ የሆነ አሠራርን ለመዘርጋት ታልሞ ነው ብለዋል፡፡ ስለቅልጥፍና ሲያወሩም የቀድሞው ሕግ ወይንስ ያሉን ተቋማት ናቸው ፍትሕ እንዲያዘግም የሚያደርጉት የሚለው ሊጤን እንደሚገባ በመግለጽ ቀደም ብሎ የነበረው ሕግ ጉድለት ምን እንደሆነ? ጉድለቱንስ ማስተካከል የሚቻለው አዲስ ሕግ በማውጣት ነው? ወይንስ አይደለም? በማለት መመርመር እንደሚያስፈልግ ጠቁመው እንደእርሳቸው አመለካከት ባለሙያው እና ተቋማቱ ላይ መሠራት እንዳለበት አበክረው በመግለጽ ሁሉን ነገር በመጻፍ እና ሕግ በማውጣት ማሻሻል ለውጥ ማምጣት አይቻልም ብለዋል፡፡

ወንጀል ቢወሳሰብም፣ ቢቀልም መርሁ ያለው በአንድ ክልል ውስጥ መሆኑ የወንጀሎች መወሳሰብ አዲስ ክስተት እንዳልሆነ እና በቀድሞው ሕግ ሊፈታ ያልቻለ ቁምነገር ስለመኖር አለመኖሩ ጠይቀዋል፡፡ ይህ ረቂቅ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ ሲሆን የማስረጃ ሕግ እንደሌለን የሚታወቅ ሆኖ ዓላማው ላይ የማስረጃ ሕግ ማውጣት ማስፈለጉ የሚል ነጥብ ያልተካተተበት በመሆኑ ይኼ ቢስተካከል ብለዋል፡፡ የማስረጃ ሕጉ ለብቻው ተነጥሎ ቢወጣ የወንጀሉንም ሆነ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ላይም ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዳ ሲሆን በዚህ ምክንያት የማስረጃ ሕጐች እንደቀድሞው በየቦታው ተሰንቅረው እንዲገኙ የማድረግ ልማዳችንን አስቀጥለነዋል ብለዋል፡፡ ዓላማ የተቀመጠውም በእሳቸው እይታ አሳማኝ አለመሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎችን በተመለከተ ከሕጋዊነት መርህ ጋርም የሚያያዝ ሲሆን የሕጋዊነት መርህ በውስጡ ንዑሳን መርሆች ያሉት ሲሆን አንድ ሕግ ተመልሶ ወደኋላ አለመሥራቱ ተካትቷል፡፡ ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች በቀድሞው ሥነ-ሥርዓት ይቀጥላል፡፡ ነገር ግን ያለቁ ጉዳዮች በእዚህ አይታዩም ይላል፡፡ ነገር ግን የሥነ-ሥርዓት ሕግ ወደኋላ ተመልሶ አይሰራም ማለቱ አግባብ እንዳማይመስላቸው አበክረው ገልፀዋል፡፡

መርሆዎች ተብለው የተቀመጡ ድንጋጌዎች መኖራቸውን ጠቁመው የመጀመሪያው ነፃ ተብሎ የመገመት መብት በአንቀጽ 5 ንዑስ ቁ. 3 ላይ የሕሊና ግምት የሚለው ግልጽ አይደለም፡፡ መሆን ካለበት የሕግ ግምት ነው እንጂ የሕሊና አይደለም፡፡ ንዑስ አንቀፁ አዙሪት ያለበት ይመስላል፡፡ የድንጋጌው አቀራረጽ ትክክል አይደለም፡፡ ሌላው መርህ በአንድ ወንጀል ድጋሚ ክስን የሚመለከት ሲሆን ወንጀል በሁለት መልኩ የሚገለጽ ሲሆን አንድም በፍሬ ነገር አንድም በሕግ መሠረት ነው፡፡ አንድ ሰው በወንጀል ክስ ድጋሚ አይከሰስም የሚለው ፍሬ ነገሩን ወይስ የወንጀል ሕጉን ነው የማንደግመው ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ በአንፃሩ የፍትሐብሔር ሕጉ ላይ res judicata ግልጽ ባለ ቋንቋ ተመልክቷል፡፡ ነገር በወንጀል ጉዳይ ላይ ያለው double jeopardy ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ አይደለም፡፡ ፍሬ ነገር ሳይቀየር አንቀፁ ቢቀየር ምን ይሆናል የሚለው በግልጽ አልተመለከተም፡፡

በጠበቃ የመታገዝ መብትን በተመለከተ በመንግሥት የሚሰጠው አገልግሎት በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ አቅም ማጣት እና የፍትሕ መጓደል የሚሉ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች ያሉ ሲሆን አንድ ሰው በወንጀል ተከሶ ከባድም ሆነ ቀላል ያለጠበቃ መከራከር የፍትሕ መጓደልን ያስከትላል፡፡ ይህን የሚያባብሱ ምክንያቶች ደግሞ የፍርድ ተገማች አለመሆን፣ የሕጐች መብዛት ወዘተ... ምክንያቶች እንዳሉ ጠቅሰዋል፡፡ መንግሥት የዜጐች ደህንነት እና ጥቅም የማስጠበቅ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ለመክሰስ ባለሙያን የሚያደራጀውና የሚያሰለጥነው መንግሥት ለተከሳሹ የሚቆም እና ፍትሕ እንዲሰፍን ማድረግ የሚችል የተከላካይ ጠበቃን ቢሮን በአግባብ አለማደራጀቱ ትልቅ እንቅፋት ነው፡፡ አቅም የለኝም የሚለው የመንግሥት መከራከሪያ ውኃ ሊያነሳ አይችልም ብለዋል፡፡

ከዳኝነት ሥልጣን ጋር የተዘረዘረ ነገር በረቂቁ ውስጥ የተካተተ ሲሆን የሥነ-ምግባር ሁኔታም ጭምር የተቀመጠ ይሁን እንጂ በረቂቁ ላይ ወጣ ያለ ነገር አለ ብለዋል፡፡ በፍትሐብሔር ጉዳይ ላይ የተቀመጠ ዳኛ በወንጀል ጉዳይ ላይ ቢቀመጥ ችግር የለውም የሚል ነገር የተቀመጠ ሲሆን አንድ ዳኛ ከእዚህ ቀደም ባየው ጉዳይ ላይ መቀመጥ አይችልም ከሚለው ጠቅላላ መርህ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ይኼ ሊታይ ይገባል ብለዋል፡፡ ከእዚህ ጋር በተያያዘ ዳኛ ይነሳልኝ የሚል አቤቱታ ውድቅ

ቢሆን በይግባኝ መፍትሔ የሚሰጠው ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በይግባኝ ነው የሚለው በፍሬ ነገር ረገድ ትክክለኛ የሆነ ውሳኔ ዳኛ መነሳት ነበረበት በሚል ምክንያት ውሳኔው ሊሻር ይችላል ወይ? ብለው ጠይቀዋል፡፡

የወንጀል ክስ ወይም ጥቆማ ማቅረብ መብት ሲሆን በልዩ ሁኔታ የተወሰኑ ወንጀሎችን ደግሞ መጠቆም ግዴታ ነው ካሉ በኋላ በረቂቁ አንቀጽ 64 ሥር የተቀመጠው የግዴታ ጥቆማ የማቅረብ ኃላፊነት የሚጥሉ የወንጀል ዓይነቶችን በተወሰነ መንገድ አስቀምጧል፡፡ ይሁን እንጂ ዝርዝር ከወንጀል ሕጉ ላይ ከተቀመጡት ያነሱ ሲሆን ከተዘረዘሩት ውጪ ያሉ ከባድ ወንጀሎችን አለመጠቆም የሚያስከትለው ውጤት አይኖርም በሚል ታስቦ የተቀመጠ እና የቀድሞውን ሕግ የሚሽር ስለመሆን አለመሆን ጠይቀዋል፡፡

ከብርበራ በተያያዘ በአንቀጽ 89 ያልተፈቀደ ዕቃ የተቀመጠው ምን እንደሆነ ግልጽ ካለመሆኑም በላይ ለሌላ ዓላማ በፈቃድ ብርበራ የወጣ ሕጋዊ መርማሪ ሌላ ወንጀል የተፈፀመበትን ዕቃ ቢያገኝ ወንጀልን ከመከላከል ዓላማ በሚል የሚያዝበት ሕጋዊ አግባብንም አንስተዋል፡፡ ናሙና አልሰጥም ያለ ሰው ግምት (adverse presumption) ጥሩ ሆኖ ሳለ ናሙና አስገድዶ አካልን ተዳፍሮ መውሰድ ዓላማው ምን እንደሆነ ግልጽ አይደለም ብለዋል፡፡ አስፈላጊና ተመጣጣኝ ጉልበትም መጠቀም እንደሚቻል ያስቀምጣል፡፡ ይሁን እንጂ ይኼ ጉዳይ በእርሳቸው አመለካከት አግባብነት እንደሌለው ገልፀው አስገድዶ ከመውሰድ ይልቅ ግምት ወስዶ የማስረዳት ሸክምን ማዞር አይሻልም ወይ በማለት ከጠየቁ በኋላ ይህ አሠራር ከማስገደድ ይልቅ የሰለጠነ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በምርመራ ጊዜ በመርማሪ የሚሰጥ ዋስትና ላይ በተጨማሪነት የተወሰኑ የጥንቃቄ እርምጃዎች በወንጀል ሕጉ ላይ የተቀመጡ የቅጣት ዓይነት ናቸው፡፡ እነዚህ የቅጣት ዓይነቶችን ደግሞ ፍ/ቤት እንጂ የሚመመረምረው አካል አይደለም የሚሰጠው ብለዋል፡፡ አሁን ሥራ ላይ ያለው ሕግ መመዘኛው ሞት እና አሥራ አምስት ዓመት የነበረ ሲሆን አሁን ግን በሙስና ወንጀል ከአሥር ዓመት በላይ ለሚያስቀጡ ወንጀሎች እንዲሁም በሌሎች ሕጎችም በተመሳሳይ ዋስትና የሚያስነፍጉ ሁኔታዎች የተቀመጡ ሲሆን ዋስትና የሚከለከለው ቀላል በሆኑ የወንጀል ጉዳዮችን ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን አግባብነት የለውም፡፡ ዋስትና በመርህ ደረጃ መብት መሆኑ ቀርቶ መርሁ የመከልከል እየሆነ መጥቷል ብለዋል፡፡ ዋስትናን በተመለከተ የቀድሞው ሕግ ዋስትናን ያስከበረው ሰው/ተከሳሽ ወይም ዋሱ እንዲያስረዱ እና ምክንያታቸውን እንዲገልፁ የሚጠየቅ ሲሆን በአሁኑ ግን ዋሱ ቀርቦ እንዲያስረዳ እና አሳማኝ ካልሆነ ዋስትናው ይወረሳል፡፡ ከእዚህ ሥርዓት ይልቅ ተከሳሽ የቀረበትን ጉዳይ ተከሳሹ እንጂ ዋሱ የማያውቅ በመሆኑ ዋስ የሚሆን ሰው እየጠፋ እንዲሄድ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡

ከክርክር ውጪ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በአዲስ መልክ የተካተተ ሲሆን ማስረጃ ስላለ ብቻ ወደ ክስ ይኬዳል ማለት ግን አይደለም፡፡ የቀድሞው ሕግ ላይ አስቸጋሪ የነበረው በክስ ላይ የሚቀመጠው የክስ ጊዜ እና ቦታ መጥቀስን ይመለከታል፡፡ ክስ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ መረጃ እስከሆነ ድረስ ግልጽ መሆን አለበት፡፡ አንዳንድ ወንጀሎች ቅፅበታዊ ናቸው፡፡ ስለዚህ ይህንን በሚያስረዳ ሁኔታ ክስ መቅረብ አለበት፡፡ እንደወንጀሉ ባሕሪ ሰዓቱና ሁኔታ በአግባቡ መገለጽ አለበት፡፡ ምክንያቱም የመከላከል መብት ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥር በመሆኑ ነው፡፡ ዝም ተብሎ በአልታወቀ ቦታ እና ጊዜ ሊባል አይገባም ብለዋል፡፡ የአሁኑ ረቂቅም ይህንን ግምት ሳያስገባ ረቂቅ ሕጉም ጊዜና ቦታው ያልታወቀ እንደሆነ በሚል የምርመራ እና የክስ ሂደት ላይ ትጋት እንዳይኖር የሚያበረታታ አንቀፅ ማስቀመጡ ተገቢነት የለውም ብለዋል፡፡ ይህ ማለት ግን የጊዜ እና የቦታ አገላለጽ ችግር ያለባቸው ውስብስብ እና ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆዩ ወንጀሎች የሉም ማለት ግን አይደለም፡፡

የአማራጭ ክስ አቀራረብ ጉዳይ በሚመለከት ሲሆን በብቃት ማነስ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ፍሬነገሩን አይቶ አማራጭ ክስ ማቅረብ ይቻላል ብለዋል፡፡ the lesser included offense principle የሚለውን በመተው የቀረበው ማስረጃ ዐቃቤ ሕግ ካቀረበው ክስ በላይ የሚያስቀጣ እንደሆነ ክሱ እንዲሻሻል ይደረጋል የሚል ድንጋጌ የተካተተ ሲሆን ክስ ከተሻሻለ በኋላ ክሱ እንደአዲስ የሚታይ መሆን አለመሆኑ ከቆመበት የሚቀጥል ስለመሆን አለመሆኑ በሕጉ ላይ መካተት አለበት የሚል ጥቆማ

አቅርበዋል፡፡ በየትኛውም መንገድ ቢሆን በተገቢው ፍጥነት ውሳኔ የመስጠት ነገሩ ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል ብለዋል፡፡

ክስ በትክክል ስለመድረሱ ሳናረጋግጥ ክስ በሌለበት መስማት ነገሩን ለመድገም ነው እንጂ ሌላ ፋይዳ የሌለው መሆኑን ጠቁመው መጥሪያ አደራረሱ የፍትሐብሔር ጉዳይ አደራረስ ነው የሚመስለው፡፡ የወንጀል ኃላፊነት ከፍትሐብሔር ነገር የሚለይ በመሆኑ የመከላከል መብቱን የማለፉ ጉዳይ ሊታሰብ የሚገባው የመጥሪያ አደራረስ ሁኔታ ከፍትሐብሔር የለየነው እንደሆነ ተከሳሽ ሲቀርብ ጉዳዩን በድጋሚ መስማት፣ ምስክሮችን በድጋሚ መጥራት ወዘተ… የሕዝብ ኃብት ብክነት ነው ብለዋል፡፡

ቀጠሮ ሲሰጥ በሕጋዊ ምክንያት መሆን አለበት፡፡ ፍርድ ቤት ተቋም ነው እንጂ ግለሰብ ባለመሆኑ በሕግ በማይታወቁ ምክንያቶች ለቀጠሮ ምክንያት እየሆነ በተግባር እያየን ያለንበት ሁኔታ ያለ መሆኑን ጠቅሰው ዳኛ አለመኖርን እንደአብነት ጠቅሰዋል፡፡ ሌላው ምክንያት ምስክር ተሟልቶ አለመቅረብ ሲሆን ይህ ልማድ እየሆነ በሕግ ውስጥ አለአግባብ እውቅና እንዲቸረው ተደርጓል፡፡ ይህ ልማድ የመጣው በስንፍና በመሆኑ የspeedy trial መርህን የሚጣረስ ነው፡፡

ዐቃቤ ሕግ ምስክሮቹን የመደበቅ ድንጋጌ መካተቱ ተገቢ አይደለም ብለዋል፡፡ የመንግሥት ሥራ በግልጽነት መርህ ላይ የተመሠረተ መሆን እንዳለበት ሕገ መንግሥቱ የሚያስቀምጥ ሲሆን በቂ ምክንያት ሲኖር ተከራካሪ ወገኖች ከተከራከሩ በኋላ ምስክሮችን የመደበቅ ሁኔታ ግን የግልጽነት መርህን ያሚላ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በአንቀጽ 287 ላይ በጐ ነገር ተካቷል ያሉት ጽሑፍ አቅራቢው ምስክር በጣቢያ የሰጠው ቃል እና በፍርድ ቤት የሰጠው ቃል የተለያየ ሲሆን ተከሳሽ ምስክሩን impeach ለማድረግ ይጠቀመዋል፡፡ የእኛ ሥርዓት በከፊል adversarial በከፊል inquisitorial ነው ተብሏል፡፡ ፍርድ ቤቶቹ ጥያቄ በሚጠየቅበት ወቅት ጣልቃ ገብቶ ውድቅ የሚያደርጉበት ሥርዓት አግባብ አይደለም ብለዋል፡፡ በመጨረሻ ግልጽ እና አሳማኝ የሚለው የማስረዳት ምጣኔ በጥናት የተደገፈ መሆን አለበት ካሉ በኋላ በረቂቅ ሕጉ ላይ ያዩአቸው ክፍተቶች እነዚሁ መሆናቸውን በመግለጽ ደምድመዋል፡፡

## <u>አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - መድረክ አመቻች</u>

አቶ ኑሩ ሠይድ ያቀረቡትን ትችታዊ ጽሑፍ በማድነቅ ጭምር ያመሰገኑ ሲሆን፣ እርሳቸው ያቀረቡት ጽሑፍ ግልጽ በመሆኑ በድጋሚ ለማሳጠር የማይፈልጉ መሆኑን ገልፀው አሁን ባለው የሕግ ሥርዓት ችግሮችን ለመፍታት አንችልም ወይ በሚለው የፍልስፍና ጥያቄ የተጀመረው ጽሑፍ በረቂቁ ላይ የተቀመጡ ዝርዝር ሕጐችን በማየት እና በክፍተቶቹ ላይ ትችቶችን በመሰንዘር ለረቂቁ ማሻሻያ ግብዓት የሚሆኑ ኃሳቦችን አንስተዋል፡፡ በመጨረሻም የሞት ቅጣትን በተመለከተ ረቂቅ ሕጉ ዝርዝር እና አስቸጋሪ ድንጋጌዎችን ያስቀመጠ ሲሆን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ሂደቶችን ግምት ያላስገባ ስለመሆኑ ጠቁመዋል፡፡

## <u>አሌክሳንድራ ፎስተር - ጽሑፍ አቅራቢ</u>

ሚስ አሌክስአንደር ፎስተር ከአሜሪካ ኤምባሲ የመጡ ስለመሆናቸው እንዲሁም በሀገራቸው ረዥም ዓመታት በአቃቢ ሕግነት ሲያገለግሉ መቆየታቸውን በዝርዝር ከገለፁ በኋላ በዚህ መድረክ ላይ የጥፋተኝነት ድርድር በአሜሪካ ምን እንደሚመስል በዝርዝር ያስረዱ ሲሆን የጥፋተኝነት ድርድር ለፍርድ ቤቶች፣ ለአቃቤ ሕግ መ/ቤቶች፣ ለተከሳሾች፣ ለግል ተበዳዮች እንዲሁም ለጠቅላላው ማኀበረሰብ ያለውን ጥቅም ዘርዝረዋል፡፡

ፍርድ ቤቶችን አስመልክቶ የሚቀርቡላቸውን ጉዳዮች በፍጥነት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲወስኑ የሚያስችል መሆኑን፤ የኬዞችን ክምችት የሚያስወግድ እና ለፍ/ቤቶች ነባሪ የሚከፈለውን ወጪ የሚቀንስ መሆኑን እንዲሁም የፍርድ ሂደት ጊዜን የሚቆጥብ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ለአቃቢ ሕጎች የወንጀል ጉዳዮች ብዛትን የሚቀንስ መሆኑን እንዲሁም ውስን የሆነውን ሐብት ክርክር ለሚሹ ጉዳዮች እንዲመደቡ ከማስቻሉም በላይ ውጤታማ በሆነ መልኩ ጉዳዮች በፍጥነት

እንዲፈቱ መልካም አጋጣሚ ፈጥረዋል ብለዋል፡፡ ለተከሳሹ ደግሞ ቅጣትን በመቀነስ የሚረዳ ሲሆን ለግል ተበዳዮች በአንፃሩ ጉዳት ያደረሰባቸው ሰው ከቅጣት ያላመለጠ በመሆኑ በፍትህ ሥርዓቱ ላይ ያላቸውን ተአማኒነት ይጨምራል ብለዋል፡፡ በመጨረሻም ለማኅበረሰቡ የተሻለ የጋራ መግባባትን የሚፈጥር እና ወደ ፍ/ቤት ሲኬድ ሊያስከትል የሚችለውን ድካም እና ወጪ ይቀንሳል፡፡

በጥፋተኝነት ድርድር ላይ የሚቀርቡ የተለያዩ ትችቶች ያሉ ሲሆን ከእነዚህ መካከልም ሕገ መንግሥታዊ የመሰማት መብትን የሚያስቀር መሆኑ፣ ንፁህ የሆኑ ሰዎች ያለአግባብ እንዲያምኑ የሚያደርግ መሆኑ፣ የግል ተበዳይን ከፍትህ ሥርዓት ሒደት ውጪ የሚያደርግ መሆኑ፣ በድርድር ውስጥ ወንጀለኛው ያነሰ ቅጣት እንዲተላለፍበት የሚፈቅድ በመሆኑ የሚሉት ይገኙበታል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ትችቶች ውሃ እንደማያነሱ የተለያዩ ጥናቶች ያስረዱ ስለመሆናቸው በዝርዝር አስረድተዋል፡፡ ትችቶቹ መሠረት የሌላቸው ስለመሆናቸው የተለያዩ ተጨባጭ ጉዳዮችን በማንሳት ተንትነዋል፡፡

## ሮበርት ዋግነር - ጽሑፍ አቅራቢ

ሮበርት ዋግነር በኬንያ ካለው የአሜሪካ ኤምባሲ የመጡ መሆናቸውን ጠቅሰው በሥራ ዘመናቸው የፕሮቤሽን ኦፊሰር፣ አቃቢ ሕግ፣ ረዳት ጠቅላይ አቃቤ ሕግ፣ የወንጀል ጉዳዮች የግል ጠበቃ እንዲሁም በፌደራል ተከላካይ ጠበቃ ቢሮ ሱፐርቫይዘር በመሆን ያገለገሉ ስለመሆናቸው ገልፀው የጥፋተኝነት ድርድርና ስምምነት በሀገራቸው ጉልህ ስፍራ የሚሰጠው መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ብዙ የወንጀል ጉዳዮች እልባት የሚያገኙት በዚሁ ሥነ ሥርዓት ነው፡፡ የወንጀል ተከላካይ ጠበቃ ሁልጊዜም የሚጥረው የተሻለ ውጤት ለማምጣት ነው፡፡ በአሜሪካ ውስጥ የወንጀል ክስ ጥቆማ የቀረበባቸው ሰዎች በድርድሩ መሠረት ቅጣት ዝቅ የሚልበት አሰራር ለረዥም ጊዜ ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ የጥፋተኝነት ድርድር ለተከሳሽ ዘርፈ ብዙ የሆነ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን ከነዚህም መካከል ከፍርድ በፊት ያለ በማረፊያ ቤት የመቆየት ልማድን የሚያስወግድ፤ የተጠርጣሪዎችን ያልተገባ ጭንቀት እንዲሁም አለመተማመን ከማጥፋቱም በላይ ቅጣት ባመኑት መሠረት እንዲቀልላቸው በማድረግ የሚያግዝ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

የጥፋተኝነት ድርድር ውጤታማ በሆነ ሁኔታ የሚያገለግለው በተለያዩ የግድያ ወንጀሎች፣ ዕፅ በማዘዋወር ወንጀሎች፣ በፆታዊ ጥቃት ጉዳዮች፣ ስርቆት እና በመሳሰሉት ሲሆን ወደ ጥፋተኝነት ድርድር መካሄድ የሌለባቸውን ሁኔታዎች ጭምር ዳሰዋል፡፡ ተጠርጣሪ ንፁህ ወይም ወንጀል አለመፈፀሙን ፍንጭ የሚሰጥ ማስረጃዎች በተወሰነ መልኩ ሲገኙ፤ አቃቤ ሕግ ያቀረበው የቅጣት መጠን በፍርድ ቤት ሊወሰን ከሚችለው ቅጣት ጋር ሲነጻጸር ተከሳሽን የማይጠቅም ከሆነ፤ ተጠርጣሪው ለመደራደር ፈቃደኛ ካልሆነ ወይንም ደግሞ በአቃቤ ሕጉ አቋም ላይ ጥርጣሬ ሲኖረው፤ ወይም ተከላካይ ጠበቃው እና ተጠርጣሪው ፍ/ቤት በመሄድ የተሻለ ጥቅም ይገኛል ብለው ሲያስቡ የጥፋተኝነት ድርድር አይመከርም ብለዋል፡፡

የወንጀል ጉዳዮችን በጥፋተኝነት ድርድር ለመፍታት በሚደረገው ሥነ ሥርዓት ውስጥ ተጠርጣሪውን እና አቃቤ ሕጉ በዋናነት ተሳታፊ ሲሆኑ ተከላካይ ጠበቃም በመካከላቸው ይገኛል፡፡ የጥፋተኝነት ድርድር በጉዳዩ ላይ ጥልቅ እውቀትን የሚሻ እና ምክክር የሚፈልግ ጉዳይ ነው፡፡ ስምምነቱ ሕዝባዊ ሰነድ ሆኖ ለሕዝብ ግልፅ በሆነ አግባብ ተፈርሞ ይቀመጣል ካሉ በኋላ በቀረቡጽ ጽሑፎች ላይ ተሳታፊው ሀሳብ አስተያየቱን እንዲሰጥ መድረኩ ተከፍቷል፡፡

## ፋሲል ስለሺ

እስካሁን የጥፋተኝነት ድርድርን የሚፈቅድ ሕግ የሌለን ሲሆን ረቂቅ የወንጀል ሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ ላለፉት አሥርት ዓመታት ረቂቅ ሆኖ ቆይቷል ካሉ በኋላ የጥፋተኝነት ድርድርና ስምምነት በፍትሐብሔር ጉዳይ ላይ ጠቀሜታው ምን እንደሆነ እንዲብራራላቸው እንዲሁም ድርድሩ መደረግ ያለበት ትክክለኛ ጊዜ መቼ እንደሆነ ጠይቀዋል፡፡ በተጨማሪም አሁን ያለው ሥርዓት እና

ልማድ የወንጀል ጉዳይን የሚመረመርው አካል እና ክስ የሚያቀርበው ወገንተኛ በመሆን የግል ተበዳይን የመወከል ሁኔታ ያለ በመሆኑ ምን ዓይነት ሥርዓት ማቋቋም ጠቃሚ ይሆናል በማለት ጠይቀዋል፡፡

## ሮበርት ዋግነር

የኛ ሀገር የሕግ ሥርዓት እውነት በመፈለግ ላይ የማያተኩር ነው የምትሉ እንደሆነ አሁን ያለውን የፍትሕ ሥርዓት ባህል ማሻሻል እና አዳዲስ ሀሳቦችን በማምጣት የማኅበረሰቡን እምነት ማግኘት ይቻላል ብለዋል፡፡

## አሌክሳንድራ ፎስተር

ረቂቅ ሕጎች ረዘም ላለ ጊዜ ሳይፀድቁ የመቆየቱ ነገር በኢትዮጵያ ሳይሆን በሌሎች ሀገራትም የተለመደ ነው፡፡ የጥፋተኝነት ድርድር እና ስምምነት አያሌ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን በተጠርጣሪው ላይ የቀረበውን ጥቆማ የሚያስረዳ ማስረጃዎች በሙሉ ከተሰበሰባ በኋላ ድርድሩ ሊኪናወን የሚችል ቢሆንም ለተጠርጣሪው የሚጠቅመው ግን የምርመራው ስራ በተጀመረበት ጊዜ ያለው ነው ምክንያቱም የድርድሩ ዓላማ አንድም ውስን የሆነውን ሀብት መቆጠብ በመሆኑ ጥፋተኛ ሊያሰኙ የሚችሉ ማስረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ በድርድሩ አማካይነት ሊድን የሚችለው የሕዝብ ሀብት አናሳ ነው ብለዋል፡፡

በአቃቤ ሕጉ እና በተከላካይ ጠበቃው መካከል ያለው ግንኙነት አና መተማመንን አስመልክቶ ሁለቱም ወገኖች ክብራቸውን ከሚያጎድፍ ማንኛውም አሰራር በመቆጠብ የሚሰሩ በመሆኑ ድርድሩ ለሁለቱም ወገኖች የተሻለ ጠቀሜታን ያስገኛል፡፡ በዚህ መተማመን ውስጥ አቃቤ ሕግ ያገኛቸውን እያንዳንዱን ማስረጃዎች ለተከላካይ ጠበቃው የሚያሳይ እና የሚያስረዳ ሲሆን በተመሳሳይ መልክ ተከላካይ ጠበቃውም ከአቃቤ ሕጉ የተሻለ ማስረጃ ያለው ስለመሆኑ በማሳየት ከክስ በፊት ጉዳዩ በድርድር እንዲያልቅ እና የተሻለ ፍትህ እንዲሰፍን ያስችላል፡፡ በመጨረሻም የድርድሩ ውጤት በፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ አዳጋች እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

## ታምራት ኪዳነማርያም

የአቃቤ ሕግን ሰፊ የሆነ ፈቀደ ስልጣን የሚገድብ ሕግ መኖር አለመኖሩ ከጠየቁ በኋላ አንድ ተጠርጣሪ የወንጀል ድርጊቱን አምኖ በማናቸውም አግባብ የወሰደውን ንብረት ወይም ያገኘውን ጥቅም ከመለሰ ከቅጣት የሚድንበት የሕግ አግባብ አለ ወይ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ በመጨረሻም በረቂቅ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ላይ ፍርድ ቤቶች በጥፋተኝነት ድርድር ውስጥ ሚና ያላቸው ስለመሆኑ ካለመጠቆሙ ጋር ተያይዞ በዚህ ጉዳይ ላይ ያላቸውን አስተያየት ጠይቀዋል፡፡

## ሮበርት ዋግነር

እንደ ተከላካይ ጠበቃ አቃቤ ሕግና ተከላካይ ጠበቃ ከተስማሙ የፍርድ ቤት ድርሻ ድርድሩን ማፅደቅ እና መቀበል ይሆናል፡፡ ይህ የድርድሩን መፈጸም ተአማኒነት ይበልጥ ያረጋግጣል፡፡

## ቀለመወርቅ ሚዴቅሳ

በእርሳቸው አመለካካት በጥፋተኝነት ድርድር ውስጥ የሥነ ሥርዓት ግድፈት ያለ መሆን አለመሆኑን የማጣራት እና የማረጋገጥ ኃላፊነት በቅጣት ጋይድ ላይን መሠረት የፍርድ ቤቶች ስልጣን በመሆኑ ስምምነቱን ሊሽረው ይችላል ብለዋል፡፡

## አሌክሳንድራ ፎስተር

በአሜሪካ የጥፋተኝነት ድርድር ስምምነትን የመቀበል ሳልጣን የፍርድ ቤት ስልጣን ሲሆን ስምምነቱን በቀጥታ ፍርድ ቤቱ እንዲያፀድቅ ማስገደድ የፍርድ ቤቱን ቅጣት የመወሰን ነጻነት ወደ ጎን የሚያስተው እና ሊያስቆጣ የሚችል ነው፡፡ ካሉ በኋላ አቃቤ ሕጎች ሰፊ ፈቀደ ስልጣን ያላቸው ከመሆኑ

ጋር ተያይዞ በአስተዳደራዊ መንገድ የውስጥ ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ከመኖሩም ባሻገር ፍርድ ቤቶች እና የተከላካይ ጠበቃ ቢሮ እንዲሁም የጠበቆች ማኅበራት ከውጭ ሆነው የሚቆጣጠሩ ናቸው በማለት አብራርተዋል፡፡

## ቴዎድሮስ ምህረት

በቅርቡ ዘ ኢኮኖሚስት ላይ የጥፋተኝነት ድርድር ጉዳይን አስመልክቶ በፍትሐዊነቱ ላይ ትችት ሲሠነዘርበት እና ተጠርጣሪ ምስክሮችን በጉቦ የሚያባብልበት እንደ ችግር መነሳቱን ጠቁመው በጥፋተኝነት ድርደር እና ስምምነት የሚገኘውን ጥቅም እና ንፁህ ሰዎች በክርክር ሂደት ውስጥ ሊያገኙት የሚችሉትን ነፃ የመውጣት ዕድል እንዴት ሚዛናዊነቱን ማስጠበቅ ይቻላል ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ በተጨማሪም የጥፋተኝነት ድርድር ስምምነት የሚሠረዝበት አግባብ ስለመኖሩ ጠይቀዋል፡፡

## ሮበርት ዋግነር

ንፁህ የሆኑ ሰዎች ቀድሞውኑ ወደ ጥፋተኝነት ድርድር ውስጥ እንዳይገቡ የሚደረግ ሲሆን ንፁህ የሆኑ ሰዎች ላይ ጥቆማ የቀረበ እንደሆነ በአብዛኛው ጊዜ ወደ መደበኛው የፍርድ ቤት ክርክር እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም የጥፋተኝነት ድርድር በስምምት ሊሻር ወይም ሊሰረዝ የሚችለው ስምምነቱ የተገኘበት አግባብ እና ሂደት በስህተት ወይም ባልተገባ ጫና የሆነ እንደሆነ ነው ብለዋል፡፡

## አቶ ስሜነህ ኪሮስ - ጽሑፍ አቅራቢ

አቶ ስሜነህ ኪሮስ ከወንጀል ክስ ሂደት ውጪ ባሉ አማራጮች ላይ አጠር ያለ ጽሑፍ ያቀረቡ ሲሆን በፍትሐብሔር አማራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶች በሚል ፈጣን ወጪ ቆጣቢ፣ ምሥጢር ጠባቂ የሆነ ሥርዓት ያለን ሲሆን ይህንን ዓይነት አሠራር ወደወንጀል ጉዳዮች በማምጣት ልንገለገልበት እንችላለን ወይ ከሚል ጥያቄ የጀመሩ ሲሆን አሠራሩን ከማምጣታችን በፊት መሠረታዊ ነገሮችን ማሟላት የሚገባን ሲሆን፣ ከእነዚህ መካከልም ገለልተኛ የሆነ ፍ/ቤት እና ጠንካራ የሆነ የዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት ያስፈልጋል፡፡ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓታችን እጅግ በጣም ሰፊ እና ውስብስብ ይሁን እንጂ ብዙ ባለሙያዎች በዚህ አግባብ አያዩትም፡፡ በወንጀል ጉዳይ ተከራካሪው መንግሥት እና ግለሰብ ሲሆን ሕጉን የሚያወጣው መንግሥት መሆኑን፣ ክርክሩ በድርድር አቅም በማይመጣጠኑ ወገኖች መካከል መሆኑን እያወቅን ይህንን ይዘን ድርድር ወደሚባለው ጨዋታ መግባት በደንብ መጤን የሚገባው እንደሆነ ገልፀው ፈረንጆቹ እንደሚሉት የጥፋተኝነት ድርድር የማይነቀፍና እንከን አልባ እንዳልሆነ መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ሙሉ የሆነ የክስ ሂደትን ለመተው አያሌ ቅድመ ሁኔታዎች ያስፈልጋሉ ብለዋል፡፡ የእኛ የክስ መስማት ሂደት እንደኮመን ሎው አገራት ረዥም ጊዜ የሚወስድ አይደለም፡፡ በመሆኑም አማራጭ በሚል የምናመጣው ጊዜን ከመቆጠብ አኳያ ያለው ጠቀሜታ ምን እንደሆነ ግልጽ አይደለም ብለዋል፡፡ በአገራችን ወጥተው ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ ብዙ የወንጀል ድንጋጌዎች ያሉን ሲሆን በማናቸውም አዋጆች ውስጥ ስንመለከት የወንጀል ድንጋጌዎችን ማየት የተለመደ ነው፡፡ በመሆኑም በፐብሊክ ፖሊሲ ላይ መጠነ ሰፊ ውይይት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ አንድን ድርጊት ወንጀል ስናደርግ ዓላማና እና በቂ ምክንያት ሊኖረን የሚገባ ሲኖረን የሕግ አውጪው አካል ግን ይህንን ሥራ በአግባቡ እየሠራ አይመስለኝም ብለዋል፡፡ ሕግ አውጪው የወንጀል ቅጣቶችን ከማስቀመጥ ይልቅ ሌሎች አማራጮችን ማሰብ ተገቢ እንደሆነ ጠቁመው የገቢዎችን አዋጅ እንደምሣሌነት ጠቅሰዋል፡፡ በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ያለን አንድ የቤዝላይን ጥናት ብቻ ነው፡፡ አሁን ያሉት ተቋማት ምን እንደሚመስሉ ማየት ተገቢ ነው፡፡ የጥፋተኝነት ድርድር ሥርዓትን ተግባራዊ ልናደርግ የምንፈልግ እንደሆነ በተለይም የተቋማት ነፃነት ላይ ነፃ እና ገለልተኛ እንዲሁም ታማኝ የሆኑ የፍትሕ ተቋማት እንዲኖረን ይሻል፡፡ ያሉብን ችግሮች ልብወለዳዊ ችግሮች ናቸው ካሉ በኋላ ዐቃቤ ሕግ ክስ ያከብዳል፣ ጠበቃ ደግሞ የማይሆን ክርክር ያደርጋል፡፡ ይህም ልማድ ወደጥፋተኝነት ድርድር ውስጥ የሚንፀባረቅ እንደሆነ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል ብለዋል፡፡

## አቶ አምሀ መኮንን - ጠበቃና የሕግ አማካሪ

በወንጀል ጉዳይ የአማራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶች የሚያስፈልግ ስለመሆኑ ጥያቄ ተነስቷል፡፡ በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ አብዛኛውን ድርሻ ይዘው የሚያጨቃጭቁት ቀላል ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆኑም በሌላ አማራጭ መታገዝ አለባቸው፡፡ አሁን ያለን የሕግ ሥርዓት ረዥም አይደለም፡፡ ነገር ግን በተግባር የሚያጋጥሙ ችግሮች አሉ፡፡ በተለይም በአደባባይ ሊተቹ የሚገቡ አንኳር ችግሮች አሉ፡፡ ሕዝብ በበዛ ቁጥር እንዲህ ዓይነት ቀላል ጉዳዮች በሥርዓት ውስጥ በመግባት ፍ/ቤት በጉዳይ እንዲጨናነቅ የማድረግ አቅም አላቸው፡፡ ሁሉንም ጉዳይ በመደበኛው የፍትሕ ሥርዓት ውስጥ በማካተት መሥራት አለብን የሚል አቋም የለኝም ብለዋል፡፡

## አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - ጠበቃና የሕግ አማካሪ

ረቂቅ የወንጀል ሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕጉ የጥፋተኝነት ድርድር ተፋልሶ ሲቀር ጉዳዩ በመደበኛው ፍ/ቤት ቀርቦ በድርድር ላይ የተገኘ መረጃ ዐቃቤ ሕግ መጠቀም እንደማይችል ያስቀምጣል፡፡ ይኼ ጥሩ ሆኖ ሳለ በባሕላዊ መንገድ ግጭቶች ለመፍታት በሚደረገው ጥረት ውስጥ የሚገኝ መረጃን ለተመሳሳይ ዓላማ እንዲውል ቢደረግ ጥበቃ አልተቸረውም ብለዋል፡፡ ሌላው ሰብዓዊ መብትን የሚጥሱ ባሕላዊ ሕጎችን ሙሉ በሙሉ ከመተው ይልቅ ያንን ጉጂ ነገራቸውን ብቻ ከውስጡ በማስወጣት ተግባር ላይ እንዲውሉ ማድረግ ለተሻለ ስኬት ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለዋል፡፡ በመጨረሻም በአገራችን ባለው የፍትሕ ሥርዓት ረቂቁን አፅድቆ ማውጣት ወይንስ ያሉንን ተቋማት እና ባለሙያዎችን የበለጠ ማብቃት ውጤታማ ያደርጋል የሚለው በድጋሚ መታሰብ ያለበት ነጥብ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

## አቶ ቀለመወርቅ ሚደቅሳ - ጽሑፍ አቅራቢ

አቶ ቀለመወርቅ ሚደቅሳ በኢትዮጵያ ወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ በአዲሱ ረቂቅ ሐግ የተካተተውን የጥፋተኝነት ድርድር እና ስምምነት በሚመለከት ጽሑፍ አዘጋጅተው ያቀረቡ ሲሆን በእጃቸው የሚገኘውን ረቂቅ ሕግ መስከረም 2009 የተሠራው የመጨረሻው ረቂቅ እንደሆነ በመጠቆም እርቅ፣ የጥፋተኝነት ድርድር እና አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ፈጣንና ፍትሐዊ የሆነ ውሳኔዎችን ለመስጠት ይረዳሉ ብለዋል፡፡ እርቅን በተመለከተ በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ፖሊሲው የተካተቱ ድንጋጌዎች ውስን መሆናቸውን ጠቅሰው ከሦስት ዓመት በታች የሚያስቀጡ ቀላል ወንጀሎች ላይ እንደሚተገበር ተቀምጧል፡፡ በግል ተበዳይና በተጠርጣሪ መካከል የሚደረግ ሰላም የማውረድ ስምምነት ሲሆን እርቅ የሚመለከታቸው ጉዳዮች በቀላል እስራት እና በግል አቤቱታ አማካኝነት የሚቀርቡ ጉዳዮችን ነው፡፡ በግል አቤቱታ ለሚቀርቡ ክሶች በድንጋጌ ውስጥ ማስገባቱ በእርሳቸው አመለካከት ትርጉም እንደሌለው ገልፀው ዐቃቤ ሕግና ፖሊስ የማግባባት ሥራ ሊሠሩ እንደሚችሉ የተቀመጠ ይሁን እንጂ ማግባባት የሚለው ቃል በአግባቡ መታየት ያለበት ይመስለኛል፡፡ እርቅ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ሊሆን የሚችል ሆኖ እርቅን በሚመለከት ያለው ክልከላ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ሲኮን ብቻ ነው፡፡

የጥፋተኝነት ድርድር ከአንቀጽ 189 እስከ 199 የተመለከተው በዋናነት ዓላማው ግዜን ለመቆጠብ ሲሆን የጥፋተኝነት ድርድር የሚከናወነው በቂ ማስረጃ ተይዞ ክስ ሊያስቀርብ የሚችል በቂ ነገር በመያዝ እንደሆነ ተቀምጧል፡፡ በመሆኑም በቂ ማስረጃ ሳይኖር ድርድር የሚደረግበት አግባብ አይኖርም ማለት ነው ብለዋል፡፡ ለጥፋተኝነት ድርድር ከሚቀርቡ ጉዳዮች መካከል በክስ ቁጥር ላይ እና በቅጣት መጠን ላይ ሊሆን ይችላል፡፡ የጥፋተኝነት ድርድር ሁለት መመሪያዎችን በተከታይነት መውጣት እንዳለባቸው ጥቆማ የሚሰጥ ሲሆን፣ የመጀመሪያው በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሚወጣ የአሠራር መመሪያ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በጠቅላይ ፍ/ቤት በኩል ሊወጣ የሚችለውን የቅጣት መመሪያ የሚመለከት ነው፡፡ ለእርቅ የቅጣት ጣሪያ የተቀመጠ ሲሆን የጥፋተኝነት ድርድር ላይ ግን ይህ ዓይነት የቅጣት መጠን ገደብ አልተቀመጠም፡፡ በመሆኑም በማናቸውም ወንጀሎች ላይ ድርድር ሊደረግ

እንደሚችል መረዳት ይቻላል ብለዋል፡፡ በድርድር ሂደት ውስጥ ብዙ ሕገ-መንግሥታዊ መብቶች ዘወር ሊደረጉ ስለሚችሉ በእዚህ ሂደት ውስጥም የተከላካይ ጠበቃ ተሳትፎ ሊኖር እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

የፍትሐብሔርን ጉዳይን ጨምሮ ለመደራደር የሚቻል ሲሆን ድርድሩ ዉጤታማ ከሆነ ለፍርድ ቤት ቀርቦ እንዲፀድቅ የሚደረግ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የሚያየው ነገር ቢኖር ድርድሩ ከሕግና ከሞራል አንፃር እንዲሁም ከቅጣት አንፃር ከሚወጣው መመሪያ ጋር በማየት የድርድር ሃሳቡን ሊያፀና፣ ሊሽር ወይም ሊያሻሽል ይችላል፡፡ ድርድሩ ካልፀደቀ በጋራ ወይም በተናጠል ይግባኝ ሊሉ እንደሚችሉ አልያም ዐቃቤ ሕግ ድርድሩን በመተው ወደመደበኛው ክርክር ሊሄድ እንደሚችል ያስቀምጣል፡፡

ሦስተኛውና የመጨረሻው የአማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን መጠቀም ሲሆን ይኼ የባሕላዊ ሥርዓት በመጀመሪያ ካየነው እርቅ የሚለይበት አበይት ነጥቦች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ዋነኞቹ መጀመሪያ እርቁ ከግለሰብ ጋር ሳይሆን ከጉሣ ወይም ከማኅበረሰቡ ጋር መሆኑ ነው፡፡ ሌላው ምርመራ ተጣርቶ ማስረጃዎች ተሰባስበው የሚካሄድ አለመሆኑ ነው፡፡ ከባድ ወንጀሎች ለምሣሌ እንደሙስና፣ እንደ ሽብርተኝነት እንደአስገድዶ መድፈር ወዘተ… ለባሕላዊ እርቅ የማይቀርቡ ናቸው፡፡ የባሕላዊ ሥርዓትን በተመለከተ በጠበቃ ስለመወከል አያወራም፡፡ ነገር ግን የጥፋተኝነት ድርድር ላይ የግድ የጠበቃ ውክልና የሚፈልግ ጉዳይ ነው፡፡ በአጥፊ ታዳጊዎች እና በደንብ መተላለፍ ላይ ብዙም የተለወጠ ነገር የለም፡፡

የፍትሕ ሥርዓቱን ጫና ለመቀነስ አማራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶችን መጠቀም ተገቢ ነው የሚል አቋም ያላቸው ሲሆን እኔ የእዚህ ይልቅ የአማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ጥቅም በዋናነት ውጤታማ ከመሆናቸው ጋር መያያዝ አለበት የሚል እምነት ያላቸው መሆኑን ገልፀው የተወሰኑ ባሕላዊ ሥርዓቶችን ለተሳታፊው ያስተዋወቁ ሲሆን እነዚህም፡-

የመጀመሪያው የኮንሶ ሲሆን በተለያየ እርከን ባሕላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ያሏቸው እና የባሕላዊ የግጭት አፈታት መንገዶቹ ብዙ ሕገ-መንግሥታዊ መብቶችን በውስጣቸው ያቀፉ ናቸው፡፡ በባሕል ሕጉ መሠረት ከእስራት ቅጣት በስተቀር ብዙ የእርምት እርምጃ ዓይነቶች አሏቸው፡፡ ፍትሕ የሚሰፍነው ብዙ ሥነ-ሥርዓቶችን ካለፈ በኋላ መሆኑን እና ሁለቱን ወገኖች በእኩል የሚከራከሩ የሚሳተፉ እንዲሁም የካሣ ሥርዓትን በማካተት ዘለዓለማዊ እርቅ እንዲኖር በማድረግ የላቀ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ስለመሆኑ በዝርዝር አስረድተዋል፡፡

በመቀጠልም የቦረና የጃርሱማ ሥርዓትን የዳሰሱ ሲሆን በሥርዓቱ የግራ ቀኝ አስተያየት ተሰምቶ የጉሣው አባላት ውሣኔ በማስተላለፍ እርቅ የማውረድ ካሣ የመክፈል እና በቀልን የማቆም ሥራ የሚሠራበት ስለመሆኑ በጥልቅ ዳስሰዋል፡፡ በአፋር ክልልም ተከራካሪ ወገኖች የሚቀርቡበት ክስን የሚያስሙበት በካሣ ዘላቂ ሰላም በመፍጠር ውጤታማ የሚያደርጉ ሰፊ ሥነ-ሥርዓትን የሚከተሉ ባሕላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶች አሉ ብለዋል፡፡

ባሕላዊ የአማራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ቢኖራቸውም ሕገ-መንግሥቱ ላይ የተቀመጡ መብቶችን እና መርሆዎችን ከመጠበቅ አኳያ የራሳቸው የሆነ ድክመት ያለባቸው መሆኑ እሙን ነው፡፡ በምሣሌነትም የጾታ እኩልነትን አስመልክቶ ሴት እና ወንድ በእኩል ደረጃ የማይታዩ የሚከፈለውም ካሣ ያታን መሠረት በማድረግ ልዩነቶች ያላቸው መሆኑን እንዲሁም ሴቶች በሽምግልና ውስጥ እንዳይሳተፉ ማድረጋቸው ተጠቃሽ ውስንነቶች ናቸው፡፡ ባሕላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች መንግሥት ለሚያወጣቸው ሕጐች እና መመሪያዎች ጭምር ተገቢ እንዲሆኑ በማድረግ ረቂቅ ሕጉ ላይም በተመሳሳይ ተካትተው መገኘታቸው የዚሁ ማሳያ ሆኖ የወንጀል ሕጉን ግቦች በአግባቡ ለማሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት አለባቸው ካሉ በኋላ ለተሳታፊው ጥያቄ እና አስተያየት መድረኩ ክፍት ሆኗል፡፡

## ፋሲል ስለሺ

አገራችን የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ያሏት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በእነዚህ ቡድኖች ልክ በሚባል ደረጃ ባሕላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ያሏቸው በመሆናቸው ከላይ የተዘረዘሩት ሦስት ሥርዓቶች ለእዛ ማኅበረሰብ ብቻ ከሚያገለግሉ በቀር በሌሎቹ ላይ ተግባራዊ ማድረግ ከባድ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በረቂቅ ሕጉ ላይ የተመለከተው የሁሉንም ቡድኖች ሥርዓት ጥቅም ላይ እንዲውል የሚያደርግ ነው? ወይንስ የተወሰኑትን ተቀብሎ በሌሎቹ ላይ ተግባራዊ የሚያደርግ ነው ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

## አቶ ጌዴዎን

የሕግ ብዝኃነት በአገራችን ያለ ሲሆን አሁን ያለው የሕግ እና የፖለቲካ ሥርዓት የባሕል ሕጐችን ከሕገ መንግሥቱ ጋር እስካልተጋጩ ድረስ የሚያስተናግድ ነው፡፡ አንድ አካባቢ ላይ የሚኖረው ሰው የራሴ ነው የሚለው sense of justice አለው፡፡ እዚህ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በባሕላቸው እና በሚያውቁት ሥርዓት መመራታቸው ምንድን ነው ችግሩ? ፍትሕ አግኝተናል ብለው የሚያስቡት በራሳቸው ሥርዓት ሲሄዱ ነው፡፡